ፓኖራማ ቁጥር 56

የትዝብት አድማስ

ታህሣሥ..... ቀን 2001 ዓም

## የዳያስፖራውን ትግል ውጤታማ ለማድረግ

ዛሬ በዓለም ዙሪያ የተሰራጨው የኢትዮጵያ ስደተኛ ማህበረ ሰብ ቁጥሩ በበርካታ ሚሊዮን እንደሚገመት ተደጋግሞ ይነገራል። በዕርግጥ ትክክለኛውን አሃዝ ለማወቅ በስታትስቲክ የተደገፈ መረጃ ባይቀርብ፥ ከመላ ጎደል ይህ ግምት የተጋነነ እንዳልሆነ ግን ሁሉም ይስማማበታል። ታዲያ ይህን ያህል ቁጥር ያለው ስደተኛ በመላው ዓለም መሰራጨቱ ብቻ ሳይሆን፥ የወያኔን ዘረኛ ሥርዓትም ተፃርሮ በመቆም የተባ ተቃውሞ ማድረጉ የታወቀ ከሆነና፥ ብሎም አነሰም አደገ ተመሳሳይ ሀገራዊ አጀንዳ የሚያራምድ ከሆነ፥ ለምን ሁሉም በተቀናጀና በተደጋገፈ መልክ ተባብሮ ያመረቃ ውጤት ሊያስመዘግብ አልቻለም? የሚል ጥያቄ የሁሉንም አዕምሮ ሲከነክነው ቆይቷል። የዚህ ኃይልና ጉልበት በቀላሉ የሚገመት ባለመሆኑ፥ ሁሉም በየቤቱ ቢትከነከንና ቢቆጭ አይፈረድበትም። በተወሰነ ብሔራዊና መሠረታዊ አጀንዳ ላይ እንኳን በተቀነባበረና በተቀናጀ ፕሮግራም ዙሪያ አብሮ መሥራት ቢችል፥ ከሀገሩ ሊያሰድደው የበቃውን ዘረኛ አምባገነን ሥርዓት ለመለወጥ ማዕከላዊ ሚና ሊጫወት እንደሚችል ለክርክር የሚቀርብ አይሆንም። የፖለቲካ ድርጅቶች መተባበር ያቃታቸውን ተግባር፥ እንዴትስ የዲያስፖራው ማኅበረ-ሰብ እንዲሰራ ይጠበቅበታል? የሚለው ጥያቄ፥ ህጋዊና ዓይነተኛ መሆኑ ባይካድም፥ እነገሌ ካልሰሩት፥ ማንም ሊሰራው አይችልም ወደሚል ድምዳሜ መድረስ፥ብሔራዊ ኃላፊነትንና ተጠያቂነትን ወደ ሌላው እንደማንከባለል ይቆጠራል። ይህ ደግሞ የእያንዳንዱን ዜጋ የተግባር ድርሻና ብሔራዊ ተልዕኮ በቀላሉ እንደማየት ይቆጠራል። ሁሉም የየራሱን ተልዕኮና ድርሻ መወጣት ብሔራዊው አጀንዳውና የትግል ፕሮግራሙ አድርጎ መቆጠር ያለበት ቢሆንም፥ የሲቪክ ማኅበረሰቡ የሚያደርገው እንቅስቃሴ ከሞላ ጎደል መልክ ባለው ሁኔታ ካልተካሄደ፥ ከንቱ ልፋት ሆኖ ነው የሚቀረው።

ዛሬ በየትኛውም የዓለም ክፍል በተለያዩ ምክንያቶች እንደ ጨው ዘር ተበትኖ ያለው የኢትዮጵያ ዜጋ፥ ሀገሩ የወደቀችበትን ሁኔታ፥ እንዲያው በአርምሞ ብቻ ያየዋል ብሎ ማለት ያስቸግራል። የሁሉም ምኞቱና ጎልሙ ሀገሩ ከጥፋት ድናለት ወያኔን አስወግዶ፥ ሠላምና መረጋገትን አስፍኖ፥ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን አመቻችቶ፥ ኢትዮጵያን እያለማና እያሳደገ መኖርን ነው። ይህ ደግሞ የማይጨበጥ ተስፋና የጎልም እንጀራ አይደለም። ሁሉም የየድርሻውን አስተዋፅዖ ካደረገ በዕርግጥ የሚሳካ ነው።በየዓለም ሀገሮች የሚኖረው ዲያስፖራ  በየጊዜው በሀገራችን  ውስጥ ስለሚፈፀመው የፖለቲካ፥ የኢኮኖሚና የማኅበራዊ ችግሮች በሚመለክት ተቃውሞውን ማሰማቱን አላቆመም።  ይህ ደግሞ መደረግ የለበት በመሆኑ የሚደገፍና የሚበረታታ ነው። ማንም ዜጋ ይህ እንዳይሳከ እንቅፋት ይሆናል ተብሎ ማሰብም የሚያስቸግር  ቢሆንም፥ አንድ አንድ ተውሳኮች አይኖሩም ማለት ደግሞ አይቻልም። በዘረኞች አገዛዝ በወደቀችው ሀገራችን የሚፈፀመውን፥የሰብዓዊ መብቶች መጣስ፥ ስለ ወያኔም ልዩ ልዩ ወንጀሎች፤ ስለረሀብ፥ ስለድኅነቱ፥የሥራ ዕጦቱ፥ስለሀገራችን መሬት ለባዕድ አሳልፎ ስለመስጠቱ፥  ወዘተ.. በየወቅቱ የተቃውሞ ሰልፎች  እያደረገ የወያኔን  ወንጀሎች፥ ያጋልጣል፥ይቃወማል፥ይኮንናልም።ይህ የሕዝብ ድምፅ የሚያመጣው  ለውጥ በቀላሉ የሚታይ አይደለም።

ከዚህም ጋር ተያይዞና ተቀናጅቶ፥በወያኔ የንግድ ድርጅቶችና የፊናንስ ተቋማት ላይ የሚደረገው የኢኮኖሚ ማዕቅብ ሲታከልበት የሚያስገኝ ውጤት እንዲሁ በቀላሉ የሚታይ አይሆንም። የወያኔ  መሪዎችና ወገኖቻቸው፥ የሀገሪቱን የንግድ አውታሮች፥የመገናኛና የመጓጓዣ አገልግሎቶች፥ የግል ቸርቻሪዎች፥የአስመጭና ላኪ ንግዶችን ሁሉ ሳይቀር በስግብግብነት ተቆጣጥረው የሀገሪቱን ሁለንተናዊ የኢኮኖሚ ኅይወት  እንዳሻቸው በፈለጋቸው መንገድ እንደሚያስኬዱት ለማንም ስውር ባልሆነበት በአሁኑ ወቅት፥ ዲያስፖራው  በእነርሱ ላይ የተቀናጀ ማዕቀብ ቢያደርግ፥ ያለጥርጥር ውጤታማ ተቃውሞ ሊያስመዘግብ ይችላል። ውጤታማ ትግል ለማስገንዘብ ግን መሠረታዊ ተግባር በቅድሚያ ሊታሰብባቸው የግድ ይላል። በገጠሪቱ ኢትዮጵያ ያደገ ኢትዮጵያዊ/ት በትክክል ሊያስታውስው  እንደሚችል፥ ሁለት ዓይነት የቆየ  የአተራረስ ወይም የእርሻ  ዘዴ መኖሩን ይረዳል።በዶማ ከሚቆፈረው ሌላ ማለት ነው። አንደኛው በበሬ የሚታረሰው ሲሆን ሌላው ደግሞ በአህያ ወይም በፈረስ ነው። በበሬ የሚታረሰው፥ዕመሙን ይዞ፥ፈሩን ተከትሎ ስለሚሄደና በሬውም ማረሻውን ተክሎ ስለሚጎትተው ማረሻው ወደ አፈሩ ጠልቆ በመግባት አፈሩን ይገለባብጠውና ዘሩ የለሰለሰ አፈር በማግኘት  ስር ሰድዶ ስለሚገባ  ብቃያው የሚያምር፥ አዝመራውም የሚያጠግብ ይሆናል። በአህያ የሚታረስ ግን ሂደቱ የበሬውን ዕርሻ ተቃራኔ ነው። ውጤቱም አጥጋቢ አይሆንም። ይህን  ቀላል ንፅፅር ወደ ዳያስፖራው ጥርትና ድካም ለማመሳሰል

ብንሞክር፥ ከሞላ ጎደል ሁሉም በአንድ ግንዛቤ ዙሪያ ሊስማማበት የሚችልበት ሁኔታ ይከሰትለታል።

ወያኔዎች በምኒሊክ ግቢ መኖር ከጀመሩ አንስቶ የሰረቱን ሥራ በመቃወም፥ ዲያስፖራው ወይም በውጭ ሀገር ያለው ልክ ሀገር ቤት እንደሚኖረው ምልአተ ሕዝብ ሁሉ፥ ቁጣውንና ተቃዉሞውን በማሰማት የሚቻለውን ሁሉ አድርጓል።ገንዘብ በማዋጣት፥የተቃውሞ ሰነዶች በማዘጋጀት፥ የተማፅንዖ ደብዳቤዎች በመጻፍና በየሚኖርባቸው ሀገሮች መንግሥታት ባለሥልጣናት በማቅረብ፥ የረሃብ አድማ በማሳየት፥ የሀዘን ሻማ በማብራት፥ለቁጥር የሚያስቸግሩ የተቃዉሞ ሰልፎችን በማድረግ ጊዜውን አዕምሮውን ጉልበቱንና ገንዘቡን ሁሉ ሰውቷል። መሥዋዕት ደግሞ በየፈረጁ ስለሚሆን ዲያስፖራውም በበኩሉ የሚጠበቅበትን ተገቢውን መሥዋዕት ሁሉ ከፍሏል። የከፈለው መሥዋዕትና ያስመዘገበው ውጤት ሲመዘን ግን ሚዛኑ የተስተካከለ አይደለም። ትግሉ እንደልፋቱ ጠብ ሊል ያልቻለበት አንደኛው ምክንያት፥ የጋራ ዕቅድና ፕሮግራም፥የትብብርና የማቀናጀት፥ የግኑኝነትና የዜና ልውውጥ እጥረት እንደሆነ ብዙ ተመልካቾችና ተቆርቋሪዎች ይተቹበታል።ትችቱን ከዕውነት የራቀ ነው ለማለት ያስቸግራል።እንኳንስ በዓለም ዙሪያ ባሉ ዋና ዋና ከተሞች ያለውን የዲያስፖራ የተቃውሞ ሰልፍ በአንድ ቀን እንዲከናወን ለማድረግ ይቅርና፥ በአንድ ከተማ ውስጥ የሚገኘውን የዲያስፖራ ተቃውሞ ሁሉም በአንድ ቀን ተሰብስቦ ለማከናወን ካስቸገረ ቆይቷል። ይህ ክስተት ሊለወጥ የሚገባው እንደሆነ ብዙ ተመልካቾች ይስማሙበታል።

በመሠረቱ፥የዲያስፖራው ትግል ለሀገር ቤቱ ትግል ድጋፍ ሰጭና ወገንተኝነቱን ለማሳየት እንጅ፥ ወሳኙ ትግል የሀገር ቤቱ እንደሆነ ሁሉም የሚስማማበት ነው። ይህ ማለት ሊቀናጅ ሊተባበርና፥ሊደጋገፍ አይችልም ማለት አይደለም። በግድ ሊደጋገፍ ይገባዋል። አለበትም። ትብብሩም በአብላጫው፥ በዜና፥ በገንዘብ፥ በቆሳቁስና በዲፕሎማቲክ ዙሪያ የሚሽከረከር ቢሆን ይመረጣል።የሀገር ቤቱ ሕዝብ በግንባር ቀደም፥ የመከራው ገፈት ቀማሽ፥ የጭቆናው ቀንበር ተሸካሚ፥ የረሃብ የቸነፈሩ፥ የበሽታው የድኅነቱ፥ የውርደት የጥቃቱ ሁሉ ተሸካሚ ስለሆነ፥የወያኔን ጭካኔ የሚጋተረው እርሱ እራሱ ነው። ቀጣይና ያልተሸራረፈ ትግል የሚያደርገው የሀገር ቤቱ ሕዝብ ነው። ትግል አሸናፊ ሊሆን የሚችለውም፥ በፅናት ጭቆናን እየተጋተሩ፥ የሚያስከትለውን መሥዋዕት እየከፈሉ፥ያልተቋረጠና ያልተፍረከረከ ጥንካሬን በተግባር ሲተረጉሙ ነው። ዲያስፖራው በተለያየ ምክንያት ይህንን ሊያደረግ ባይችልም እንኳ፥ በድጋፍ ሰጭነቱ የሚያበረክተው አስተዋፅዖ ብርቱ እንደሚሆን ምንም ጥርጥር የለውም። ብርቱ ሊሆን የሚችለው ግን፥ በጋራ ቅንብርና ትብብር፥ በተመሳሳይ ዕቅድና የተግባር ቅንጅት ሲኖረው ብቻ ነው። ከተቃዋሚ ድርጅቶች እንቅስቃሴ ጋር አንድ ዓይነት ትብብርና የጋራ ትግል መንፈስ ቢኖረው ደግሞ የሚመረጥ ይሆናል። ያ ካልሆነ ደግሞ

ዲያስፖራው ሀገሩን አሁን ከወደቀችበት ማጥ ለማውጣት በግድ የዓላማና የራዕይ አንድነት ብቻ ሳይሆን፤የተግባር ትብብርም ሊኖረው ግድ ይላል፡፡ትግልን ገንዘብ ሰጥቶ በሚገኝ የምስክር ወረቀት ማባበያ  ዲያስፖራውን እናግባባለን የሚለው ከንቱ ልፋት፥ የኢትዮጵያን ሕዝብ የማሰብ ችሎታንና የአዕምሮ ብስለትን እንደመናቅ ስለሚቆጠር፥ "ያላዋጣ ይውጣ" የሚለው አሳፋሪ መፈክር በዲያስፖራው ዘንድ መሳቂያ መሳለቂያ ከሆነ ውሎ አድሯል፡፡ ትግልን በሽልማትና በሹመት ለመደለል መሞከር የትግልን ፥ መሥዋዕትነት ክብርና ዋጋ እንደማሳነስና እንደማዋረድ ይቆጠራል፡፡  የኢትዮጵያ ሕዝብ የውስጡም ይሁን የተሰደደው ዜጋ ፥ ሀገሩን ከወደቀችበት ለማዳን የሚዋደቀው፥ ከድል በኋላ  ሹመት ሽልማት፥ ሀብት ንብረት፥ ጌጥ ማዕረግ፥ ምቾትም ይሁን ወይም ከንቱ ውዳሴን አገኝበትአለሁ ብሎ አይደልም፡፡ ለሀገሩ ነፃነት፥ለራሱ ሰብዓዊ ክብርና ከሁሉም በላይ ደግሞ፥ ኢትዮጵያን ከዘረኞች የመከፋፈል አደጋ ለማዳን ነው፡፡ ከትግል በኋላ ዋጋ ይከፈለኛል /አገኛለሁ ብሎ የሚያስብ፥ በገንዘብ የተገዛ የውጭ ቅጥረኛ ወታደር እንጅ ሀገር ወዳዱ የኢትዮጵያ ሕዝብ እንዳይደለ ከልብ እናምናለን፡፡

የዲያስፖራውን ትግል ውጤታማ ለማድረግ፡-

1 ተግባሩና እንቅስቃሴው በዕቅድና በፕሮግራም ሊቀናጅ ይገባል፡፡ ለዚሁ ሁሉ ደግሞ የዓላማ አንድነት ያላቸው ሁሉ፥የቅርብ ግንኙነትና ያልተቋረጠ የዜና/የመረጃ ልውውጥ ሊኖራቸው  የግድ ይላል፡፡

2. የሁሉንም ተሳትፎ ለማካተት አስቀድሞ በቦታና በጊዜ ምክንያት የሚያስከትሉ ችግሮችን መመርመርና መገምገም አስፈላጊ ነው፡፡ መርህ ግብርና ዕቅድ ለማነኛው ተግባርና እንቅስቃሴ ወሳኝ ሚናን የጫወታሉ፡፡

3. ከወያኔ ሰላዮችና ቅጥረኞች፥ አፍራሾችና የኢትዮጵያ የውስጥም ሆኑ የውጭ ጠላቶች በማሃከላችን ሰርስረው በመግባት የአፍራሽ ተግባራቸውን እንዳይፈጽሙ መከላከልና ነቅቶ መጠበቅ  የሁሉ ግዴታና ተግባር መሆኑ መረሳት የለበትም፡፡

4. ይህንን ማድረግ ከተቻለ፥ የዲያስፖራው ትግል አምራቂ ውጤትን ከማስመዝገብ የሚያግደው ኃይል አይኖርም፡፡